# SY25-26 እና SY26-27 Benjamin Banneker ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፥ የቅበላ ሂደት መመርያዎች

ለክፍል፡ 9 እና 10

**ማስታወሻ፥** ይህ መመርያ ለSY25-26 እና SY26-27 የተማሪ ቅበላ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**ስለ Benjamin Banneker ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የቅበላ መስፈርት**: በBenjamin Banneker ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመማር ፍላጎት፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ትጋት ላላቸው እና በተለያዩ ተግዳሮቶች ውስጥ የመስራት አቅም ያላቸውን ስኬታሞች እንፈልጋለን። በጣም ስኬታማ የሆኑ አመልካቾች በGPAያቸው ላይ በሚያገኙት ስኬት ጥንካሬያቸውን የሚያሳዩ ሆነው አግኝተናቸዋል።

**ስለ Benjamin Banneker ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የቅበላ ሂደት**: Benjamin Banneker ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ በመጀመርያ የሁሉንም አመልካቾች የውጤት መግለጫ ካርዶች፣ ጽሁፎች እና የድጋፍ ደብዳቤዎች እንገመግማለን። እነዚህ ክፍሎች እያንዳንዳቸው ውጤት ይሰጣቸዋል፣ በቅበላ ሂደቱ ውስጥ ለቀጣዩ ደረጃ የአመልካች ብቁነትን ለመወሰን በብቸኝነት ጥቅም ላይ የሚውል አንድ ክፍል የለም። ከፍተኛ ውጤት ያላቸው አመልካቾች ቃለ መጠይቅ ላይ እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል።

እያንዳንዱ ክፍል ከታች ባለው ሰንጠረዥ መሰረት ውጤት ተሰጦቶት ይመዘናል። ተጋባዥ አመልካቾች ለብቁነት እንዲታሰቡ የቃለ መጠይቅ ክፍሉን ማሟላት አለባቸው። በቃለመጠይቁ አነስተኛው 12/15 ውጤት ያመጡ አመልካቿች ለቅበላ ብዙ ናቸው ተብለው ይታሰባሉ። በቃለ መጠይቁ ከ12 በታች ውጤት ላመጡ አመልካቾች፣ Banneker ብቁነታቸውን ለመወሰን ቃለ መጠይቁን ጨምሮ በሁሉም የአመልካቹ ክፍሎች ላይ በመመስረት አጠቃላይ ውጤታቸውን ያሰላላቸዋል። ብቁ የሆኑ አመልካቾች በሙሉ በቃለ መጠይቅ ውጤታቸው መሰረት ደረጃ ይወጣላቸዋል።

| የቅበላ ክፍል | ክብደት | ማሳሰቢያዎች |
|---|---|---|
| የትምህርት መስፈርት ግምገማ (GPA) | 20/50 ነጥብ | Benjamin Banneker ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደ የሪፖርት ካርድ ግምገማ አንድ አካል ሆኖ የትምህርት ውጤቶችን (GPA) ይገመግማል። አመልካቾች የSY23-24 የመጨረሻ ሪፖርት ካርዳቸውን እና የSY24-25 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ሪፖርት ካርዳቸውን ማቅረብ አለባቸው። ማመልከቻው ለቅበላ ከግምት ውስጥ እንዲገባ ሁለቱም የሪፖርት ካርዶች መቅረብ አለባቸው።<br><br>በተለምዶ፣ በBenjamin Banneker አካዳሚክ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለመግባት የተሳካላቸው አመልካቾች በሁለቱም ሪፖርት ካርዶች ላይ በሁሉም ትምህርቶች A እና B ያመጡ ናቸው። ሆኖም ግን፣ ዝቅተኛ ውጤት ያላቸው አመልካቾችም ትክክለኛው የትምህርት ድጋፍ ተደርጎላቸው ስኬታማ መሆን ችለዋል። |
| ድርሰት፥ በMy School DC ማመልከቻ | 6/50 ነጥብ | በMy School DC ማመልከቻ ውስጥ የቀረበው ጽሁፍ ተማሪው በፕሮግራማችን ላይ ያለውን ፍላጎት፣ ለማህበረሰብ ያለውን ቁርጠኝነት እና ግላዊ ትጋትን የሚያሳይ የህይወት ልምድን ለመመዘን ጥቅም ላይ ውሏል።<br><br>አመልካቾች በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቆይታቸው ወቅት በመደበኝነት ይጽፋሉ ተብሎ ይጠበቃል፤ በመሆኑም ሰዋሰው እና ቃላትን ጨምሮ ውጤት አሰጣጡ በጽሁፍ ቴክኒኮች ላይ ያተኩራል። |

<table>
<tr><td>የድጋፍ ደብዳቤዎች</td><td>24/50 ነጥብ</td><td>Benjamin Banneker ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪው በትምህርት ቤት ላይ ያለውን ልምድ በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት እና ለትምህርት ውጤታቸው አውድ ለመስጠት የድጋፍ ደብዳቤዎቸን ይጠቀማል። የድጋፍ ደብዳቤዎች ተማሪዎችን እና ተሞክሯቸውን በተሻለ መልኩ ለማወቅ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ይቆጠራሉ።<br><br>Benjamin Banneker ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሶስት (3) የድጋፍ ደብዳቤዎች የሚጠይቅ ሲሆን፣ እያንዳንዳቸውቢበዛ 8 ነጥብ ይይዛሉ። የድጋፍ ደብዳቤዎች ከተማሪው የትምህርት ቤት አስተዳደር፣ ረዳት አስተዳደር ወይም የትምህርት ቤት ካውንሰለር እና ከተማሪው የ 8ኛ ክፍል የሂሳብ እና ELA መምህራን መቅረብ አለበት። አመልካቾች እና ቤተሰቦቻቸው በነሱ ስም የድጋፍ ደብዳቤ ከሚሰጡ ግለሰቦች ጋር እንዲከታተሉ እና በተቻለ መጠን ስለተማሪው የተሟላ ምስል ማግኘታችንን ለማረጋገጥ የድጋፍ ደብዳቤ ሰጪውን የኢሜይል አድራሻዎች ትክክለኝነት እንዲያረጋግጡ በጥብቅ እናበረታታለን።<br><br>በቀረቡ የድጋፍ ደብዳቤዎች ላይ በመመስረት በግምገማ ሂደቱ ወደ ቃለ መጠይቅ ደረጃ ለማለፍ የሚያስፈልጉ ያልተሟሉ ወይም የጎደሉ የድጋፍ ደብዳቤዎችን በተመለከተ ለወላጆች ይገለጻል። ይሁን እንጂ አመልካቾች ላልተሟሉ ወይም ለጎደሉ የድጋፍ ደብዳቤዎች የማይቀጡ ሲሆን በቀረቡ የድጋፍ ደብዳቤዎች ላይ በመመስረት ወደ ቃለ መጠይቅ ደረጃ እንዲያልፉ ሊገመገሙ ይችላሉ።</td></tr>
<tr><td colspan="3">በዝርዝር በተቀመጠው የመነሻ መስፈርት መሰረት ከተቀመተው የመነሻ ውጤት በላይ ያመጡ አመልካቾች ወደ ቅበሉ ሂደቱ የቃለመጠይቅ ክፍል ይቀጥላሉ።</td></tr>
<tr><td>የቤተሰብ ቃለመጠይቅ (በቦታው በመገኘት የሚደረግ የጽሁፍ ድጋፍን ያካትታል)</td><td>15 ነጥብ</td><td>Benjamin Banneker ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመማር ፍቅር፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ቁርጠኝነት እና ለዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ትጋት ያላቸውን አመልካቾች ለይቶ በማወቅ በጥብቅ ያምናል።<br><br>የBanneker ቡድን ተመሪዎችን በገለጻ ብቃታቸው፣ በይዘታቸው እና በራስ መተማመናቸው ይገመግማቸዋል።<br><br>ብቁ የሆኑ አመልካቾች በቦታው ላይ ለሚደረግ ግላዊ የተማሪ ቃለመጠይቅ ተጋብዘዋል። አመልካቾች በወላጅ/አሳዳጊ ወይም በሌ ቅርብ የቤሰብ አባል (ከ18 ዓመት እድሜ በላይ በሆኑ) ታጅበው መምጣት አለባቸው። አመልካቾች በቃለ መጠይቁ ላይ ለመወያየት በጣም የቅርብ ጊዜያቸውን የተማሪ የውጤት መገልጫ ካርዳቸውን ለማምጠት ማቀድ አለባቸው ነገር ግን ይዘው ካልመጡ አይቀጡም።<br><br>አመልካቾች የቃለ መጠይቁ አንድ አካል አድርገው በቦታው ላይ በመገኘት የሚደረግ የጽሁፍ ድጋፍን መሙላትም አለባቸው። የጽሁፍ ድጋፉ በተማሪው መሰረታዊ/የፈጠራ አስተሳሰብ እና የጽሁፍ ክህሎት ላይ ለ ፓነሉ ተጨማሪ መረጃ ለመስጠት የሚያስችል እድል ነው።<br><br>አመልካቹን አጅቦት የሚቀርበው ወላጅ፣ አሳዳጊ ወይም የሚታመን አዋቂ ሰው ስለፕሮግራሙ የሚጠበቁ ነገሮች፣ ክፍሎች፣ ወዘተ. ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በቤተሰብ የመረጃ ፕሮግራም ላይም ይሳተፋል። አመልካቹን አጅቦ የሚገኘው አዋቂ ተሳትፎ ውጤት ለመስጠት በማናቸውም ሁኔታ ታሳቢ አይደረግም። ተማሪዎች ከሚታመን አዋቂ ጋር መቅረብ አለባቸው ወይም ቃለ መጠይቁ ለሌላ ጊዜ ቀጠሮ ይሰጥበታል።</td></tr>
</table>

**በቃለ መጠይቁ 12 ወይም ከዚያ በላይ ያመጡ አመልካቾች በሙሉ ለቅበላ ብቁ እንደሆኑ ተደርገው ይታሰባሉ።**

**በቃለ መጠይቁ ከ12 በታች ውጤት ላመጡ አመልካቾች፣ ብቁነታቸውን ለመወሰን ቃለ መጠይቁን ጨምሮ በሁሉም የአመልካቹ ክፍሎች ላይ በመመስረት አጠቃላይ ውጤታቸውን ይሰላላቸዋል።**

**ብቁ የሆኑ አመልካቾች በሙሉ በMy School DC Lottery ላይ ለውሳኔ እኩል ደረጃ ይሰጣቸዋል።**

1200 First Street, NE | Washington, DC 20002 | T 202.442.5885 | F 202.442.5026 | dcps.dc.gov